ምዕራፍ 6 part 20

የምዕራፍ 6 ማጠቃለያ

ማስመሪያን በመጠቀም ቀጥታ መስመር መስራት

- ይህ ምስል **ነጥብ** በመባል ይጠራል።

ነጥብ የጂኦሜትሪ ምስሎች ሁሉ መነሻ ነው።

- ለምሳሌ 1፡- ነጥብ ሀ እና ነጥብ ለ በማገናኘት ውስን ቀጥታ መስመር ሀ ለ እናገኛለን።



ምሳሌ 2፡- በነጥብ ሀ እና በነጥብ መ የሚያልፍ ቀጥታ መስመር መስራት እንችላለን።



ቀጥታ መስመር ሀመ

ምሳሌ3 ፡- ነጥብ ሀ ፣ነጥብ ለ እና ነጥብ መ በውስን ቀጥታ መስመር ጎነ ሶስት ምስል መስራት እንችላለን።



ጎነ ሶስት ሀለመ በመባል ይጠራል።

ምሳሌ 4፡- ነጥብ ሀ ፣ነጥብ ቀ ፣ ነጥብ ጨ እና ነጥብ መ በማገናኘት ጎነ አራት ምስል መሳል እንችላለን።



ጎነ አራት ሀቀጨመ

የቀጥታ መስመሮች እና የነጥብ ግንኙነቶች

ምሳሌ፡-



ቀጥታ መስመር ከጠ እና መፈ በነጥብ ጨ ላይ ይቋረጣሉ።

ነጥብ ጨ የመቋረጫ ነጥብ ትባላለች።

- **ጎነ ሶስት ምስል መሳል**
- ምሳሌ ፡-



- ከላይ ያሉት ምስሎች በሙሉ መጠናቸው ቢለያያዩም ጎነ ሶስት ምስሎች ናቸው።

ሳነ ሶስት ምስሎች ስያሜ የምንሰጠው በመለያያ ነጥቦቻቸው ነው።

ምሳሌ



ስለዚህ ሳነሶስት መለሰ በማለት ልንጠራው እንችላለን።



የዚህ ሳነ ሶስት መለያያ ነጥቦች መ፣ ለ፣ ሰ ናቸው።

የሳነ ሶስቱ መለያያ ጎኖቹ ውስን ቀጥታ መስመር መለ፣መሰ እና ፣ሰለ ናቸው።

ጎነ አራት ምስሎች

ይህንን ምስል ጎነ አራት መከጨሰ በማለት እንጠራዋለን።



የጎነ አራት መከጫሰ መለያያ ነጥቦች መ፣ከ፣ ጨ እና ሰ ናቸው።

የጎነ አራት መከጫሰ ጎኖች $\overline{\text{መከ}}$፣ $\overline{\text{ከጨ}}$ ፣
$\overline{\text{መሰ}}$ እና $\overline{\text{ጨሰ}}$ ናቸው።



የተቀባው ክፍል የጎነ አራት መከጫሰ ወለል(ጠለል) ነው።

አራቱም ጎኖች እኩል የሆነ ጎነ አራት ምስል ካሬ ይባላል።ምሳሌ



ይህ ጎነ አራት ምስል ካሬ ነው።ምክንያቱም $\overline{መከ}=\overline{ከጨ}=\overline{መሰ}=\overline{ጨሰ}$ ።

ተማሪዎች የቤት ስራ የምትሰሩት ልስጣችሁ (4 ደቂቃ)

1 ውስን ቀጥታ መስመር መሀ ስሩ።

2) ቀጥታ መስመር ወፈ ን ስሩ።

3) ሀ.ርዝመቱ 5ሳንቲ ሜትር የሆነ ጎነ ሶስት ምስል ስሩ።

ለ) የሰራችሁትን ጎነ ሶስት መለሰ በማለት ሰይሙ።

ሐ)የሰራችሁትን ጎነ ሶስት ምስል ወለል በመቀባት አሳዩ።